# ጀግና በምክንያትና በስራ፣ ሞኝ በእምቢታ ያሸንፋል!

ሠይፈ ደርቤ

የኢትዮጵያዊያን አሸናፊነት ከመቼውም ጊዜ በላቀ ሁኔታ እየጎላ መጥቷል፤ በሀገሪቱ ሁሉም አቅጣጫዎች እየተከናወኑ ያሉ የልማት ስራዎች በእርግጥም የሀገራችን ህዝቦች አጀንዳ ድህነትን ማጥፋት መሆኑ በግልፅ እያሳዩ ነው። ገጠሩ በምርትና ምርታማነት፥ ከተማው በኮንስትራክሽንና ኢንደስትሪ ልማት፣ አመራሩ የተፈጥሮ ሀብት ልማት ስራዎችና ክንውኖችን ተዘዋውሮ በመጎብኘት፣ አርሶና አርብቶ አደሩንም በማነቃቃት፣ ፓርላማው በየቋሚ ኮሚቴው ምን ተሰራ ምንስ ጎደለ እያለ ክትትል በማድረግ የሚያካሂዱት ሰፊና ያልተቋረጠ ክንውን ከዚህ ቀደም ከባድ መስለው የሚታዩ ስጋቶቻችን እያነሱ፣ እያዘቀጡም፣ እያደቀቁ በመሄድ ላይ መሆናቸውን እንድናስተውል አድርገውናል።

ይህን በእርግጥም እንድናይ ያስቻለን የልማት መነፅሩ ነው፤ መነፅሩን ላላጠለቀ ልማት አይታየውም፤ ይልቁንም « በምንትስ ጊዜ የነበረ ምንትስ ምንትስ እያለ ሲምል ይኖራል» እንደሚባለው በድሮ ፈረስ ላይ ሆነው ቀጣሪዎቻቸው እንዲጋልቡብን ተመቻቹ የሚሉንን እያየን ነው።

በህግ የተቋቋመች ሀገር፣ ህዝብ ያላትና ህዝቦቿ እየሰሩባት፣ እየተለወጡባት እያደጉባት ያለች ሀገር፣ ለራሷም ለአካባቢዋም ልትተርፍ ሌት ተቀን እየሰራች ያለች ሀገር፣ ልጆቹን ስሩ አልሙ ብሎ በየበረሃውና በየጥጋጥጉ ወጣቶቹን የለካ ሀገር ማየት የበቃቸው በኪሳቸው ልክ የሚያስቡ እጅግ በጣም ጥቂቶችንም እያየንና እየታዘብን ነው።

እነዚህ ከትላንት የማይማሩ ጥቂት «የእኛው ልጆች፣ የእኛው ወንድሞች፣ የእኛው አባቶች» በድህነት ደቅቀውና ተርበው የነበሩ የትላንት ወገኖቻቸው ባሳደሩባቸው ቁጭት እልህ ውስጥ ገብተው የሚሰሩ ልጆቻቸውን ስራ ለማበላሸት፣ ለማፍረስና በፀብና ብጥብጥ ለመበታተን የማይፈነቅሉት ትናንሽ ድንጋይ የለም፤ ትላልቁ ድንጋይማ የማንነታችን አሻራ ማኖሪያ ለሆነው ህዳሴው ግድብ፣ ወጣቱን ስራ ፈጣሪና ሀብት አፍላቂ ላደረጉት፣ የድንጋይን ዳቦነት ላስመሰከሩት ወጣቶች ግብዓት

መሆን በመጀመሩ ከየት አግኝተውት?

ህግና ህጋዊነት የዜጎች ሉዓላዊነት ማስከበሪያ መሆኑን በተሰወረ ህሊናቸው ማየት ተስኗቸው፣ በአማራጭ መግነን መፈለግም ቢያቅታቸው፣ ስለ ልማትና ለውጥ እየተደረገ ያለውን ስራ ህዝቡም ዓለሙም እየመሰከረ ቢያስቸግራቸው ሞኝ «እምቢኝ» ብሎ እንደሚያሸንፍ ሁሉ አመክንዮ በሌለው ህሊና ድሮአቸውን እየዘመሩ አሉ።

የመዝሙራቸው ባዶነት በሀገሪቱ በሰፊው እየተቀጣጠለ ባለው ልማት ተደፍቆ ህዝቡ የመደበኛ ጊዜ የስራና የፀረ ድህነት ትግሉን ከማጎልበት ባለፈ ማንም ልማቴን አያስቀመውም በሚል መንፈስ እየተላጋ ነው። ሰሚ ያጣ ጩኸታቸው የመቃብር አፋፍ ኑዛዜ ሆኖ ለትዝብት እያጋለጣቸውም ነው፤ የስህተታቸው ደማቅነት ጤነኝነት ከማጣት ይሆን እስኪያስብል ድረስ አስተዛዛቢ መሆንም ቀጥሏል።

በግልፅና በስውር ሊያራምዱት ለሚሹት ከንቱ ህልም የሚደረግላቸው የአንዳንዶች ድጎማ አንድም በከረፉ ቃላታቸው ብዛት ስሌት፣ በሌላም በኩል አይን ባወጣ የስፖንሰርና ማስታወቂያ ድጋፍ ይብልጥ እንድንገነዘባቸው አድርጎናል። እነዚህ ወገኖች በምስላቸው ባንዳ ይሉት የአበው ቃልን ከነትርጉሙ ሊያስረዳን በሚችል አግባብ ወለል ብለው እየታዩንም ነው።

እንዲህ እንድንገነዘባቸውና እንደ ህዝብ እንድናውቃቸው ላስቻለን ታጋሹ መንግስት ምስጋናም ገለታም ይግባውና አሁንም የመታገሱ ብዛት ቢያይል መንግስት ሳይሆን እኛ በይበልጥ እንድናወግዛቸው፣ ማንነታቸውም በሁላችንም ዘንድ እንዲታወቅ እድል ይሰጠናል።

በመብትና በዴሞክራሲ ሳይሆን መብትና ዴሞክራሲ እንዳይኖር ሁሌም በሚሸርቡት የአመፃ ስሌት አንድም በፀፀት፣ ሌላም ጊዜ በህግ ተጠያቂ እንዲሆኑ የመንግስት ትዕግስት ከዚህም በላይ ያሻል።

በፀብ ጫሪና ልማት አደናቃፊ ቅስቀሳቸው ለእኛ ወይስ ለማን ሲታገሉ ነበር የሚለውንም በስፋት የምናየው አሁንም መንግስት ከዚህም በላይ ሲታገስ ነው። ለነገሩ መንግስት በትዕግስት ብቻ ሳይሆን ከህዝብ ጋር በስራ ተጠምዷልና ከመታገስ ውጪ አማራጭ የለውም።

ለህዝቡም ለአካባቢውም ሰላም አዲስ አበባ ላይ ብቻ ሳይሆን በመላው የሀገራችን ክልሎችና

በአካባቢው ሀገራት ሰፋፊ ስራዎችን እየሰራ ነው። በሃይል ልማት ትስስር የደመቀው የጉርብትናና የመልካም ግንኙነት ዲፕሎማሲ መተማመን በመፍጠር፣ ሌሎች ወደ እኛ እንዲያዩም በማድረግ ከመጠንከር አልፎ ለነጋችን የምንለው ቅርስና ውርስ እያኖረልንም ነው።

ዛሬ ሰርተን ለነገ ብቻ የምንጠቀም ሳይሆን በዛሬ ስራችን ዛሬን ኖረን ነገ ለሚፈጠረው ትውልድ እንድንሆን ምቹ ሁኔታዎች አሉን። የሁላችንም ይሁንታና ፍቃድ የሆነው ህገመንግስታችንን ጨምሮ እሱን ተመርኩዘው የወጡ የሀገራችን ፖሊሲዎችና ህጎች መከበር ዛሬ ለደረስንበት፣ ነገም ለምናሳካው ግብ መሰረቶች ናቸው። ህጎቹን ተመርኩዘው የተቋቋሙ መስሪያቤቶችና አስፈፃሚዎች ስራቸውን በአግባቡ እንዲያከናውኑ ማገዝም የስኬቶቹን ጉዞ ቀልጣፋና ምቹ፣ ለህዝብም የሚጠቅም እንዲሆን የበለጠ ያስችላል።

ይህን ሀቅ ወደ ጎን ብለው በማንአለብኝነት ድርብ ድርብርብ የሆኑ ስኬቶችን በአጥፍቶ መጥፋት ብሂል ለማኮላሸት የሚሞክሩ ሃላፊነት የማይሰማቸው እንጭጭ ብዕሮች ፍሬ ባይኖራቸውም አሰልቺነታቸው ያበሳጫል። የባከኑት ጊዜያትና በውጭ ምንዛሬ የሚገዙ ቀለሞችና ወረቀቶች ብክነት አጉል መሆንም ያሳዝናል።

መሞት፣ መበታተንና መጥፋት መብት ነው ብሎ ለሚከራከር ሞኝ ይህን ማስረዳት ከባድ ነው። ከዚህ የመሞትና አጥፍቶ የመጥፋት መብት ከሚገኝ የዴሞክራሲ ልፈፋ፣ ፊደሉ ያረፈበት ወረቀትና ጊዜ ይበልጥ ጎልቶ፣ ደምቆም ይታያል። ከፊደሉ ይልቅ የመፅሄቱ፣ የጋዜጣውና የድረ ገፁ ቁመና ይበልጥ ደምቆም ይታያል። ይህ እንዲሆን ያደረገው የመፃፍ መብትን በአግባቡና በኃላፊነት መጠቀም ያለመቻል ነው።

ለግል መሞት መብት ቢሆንም «መብት ከሆነ» አብረን መሞትና መበታተን አለብን ብሎ ተነስ ማለት መብት ሊሆን አይችልም። ከመበታተኑና ከመሞቱ የሚገኝ ውጤት ማሳየት የማይችል «እብድ ብዕር» እንጂ ህዝብ ፈዋሽ፣ ዴሞክራሲና ልማት ቀያሽ ሊሆን ከቶ አይችልም። ለልማት እንነሳ፣ የሚገድለንን ዋነኛ ጠላት ድህነት እናጥፋ ሲባል «የለም እምቢ ብለን እንሙት» ብሎ የዳቦና የዲሞክራሲ አማራጭ የማያቀርብ ብዕር ስለዴሞክራሲ ሊለፍፍ፣ ሊገልጽም አይችልም።

እርግጥ ነው የእንዲህ አይነት ብዕር ፈጣሪዎች በስፖንሰሮቻቸው ድጎማ ብዙ ዳቦም፣ ብዙ ጫትም በልተው ይሆናል፤ በእነሱ ዴሞክራሲና ዳቦ አብረው አይሄዱም ተብሎም ተነግሮ ይሆናል። ሰላም ጠፍቶ ዴሞክራሲ እንዲጨልም፣ የለማውና የተገነባው እንዲፈርስ ዕለት ዕለት የሚጎተጉት የሽብር ሃይል የዴሞክራሲ ሰባኪ ሊሆን እንዴት ይችላል ጎበዝ?

ዴሞክራሲና መብትን የሚያውቅ ቀድሞውኑ የህዝብ መብት ያከብራል። የህዝብ መብትና ፍላጎት፣ ይሁንታ መገለጫ የሆኑ ህጎችን ያከብራል። ሌላው እንዲያከብርም ይታገላል። ህዝብ የሰጠውን ውክልናም ያከብራል።

ፍላጎቱንና ጥያቄውን በህግና በህግ ብቻ ለመፈፀም ይሰራል። ህግና የህግ የበላይነት በሀገሪቱ እንዲሰፍኑ ይታገላል። ህገወጥ ድርጊትን አጥብቆ ይኮንናል፤ ለአንዲትም ሰው ነፍስ ቢሆን ዋጋ ይሰጣል። ኃላፊነት ይሰማዋል፣ በኃላፊነትም ይሰራል። በሀገር ሉዓላዊነትና በህዝብ ጥቅም ጉዳይ አብሮ ይሰለፋል፣ ይቆማል።

ከዚህ በተቃራኒ አማራጭ ማቅረብ የማይችል የአቋራጭና የእጅአዙር ተንቀሳቃሽ «ዕቃ» ሀገርንም፣ ህዝብንም ራሱንም እንዲያከብር ባይጠበቅም፣ የህግ የበላይነት የህዝብ የበላይነት መሆኑን ተረድቶ ራሱን ከጥፋት ቢያቅብ ይጠቀማል። በሚያደርሳቸው የትኛዎቹም ጥፋቶች ልክ ተጠያቂ እንደሚሆን ከወዲሁ ቢገነዘብም ከውርደት ይድናል።

አላግባብ የተበላ እንደሚተፋ፣ እንደሚያዋርድና የታሪክ ተጠያቂ እንደሚያደርግ ቀድሞውኑ መገንዘብ ብልህነት መሆኑ ሀቅ ሆኖ ጊዜው እጅን ሰብስቦ እንኳ ለመቀመጥ ፋታ የማይሰጥ፣ የሞራልና የታሪክ ተጠያቂ የሚያደርግ መሆኑን በመረዳት የሀገራችን ህዝብ ከዳር ዳር እየተሳተፈበት ባለው ታላቅ የልማት ዓርማ ስር መረባረብን አማራጭ ቢያደርገው ነገ ለልጆቹ የሚያወራው ታሪክ ይኖረዋል።

በልማቱ እየለማን፣ በስራው እየተጠቀምን፣ በመንገዱ እየተጓዝን፣ አርሶ እና አርብቶ አደሩ ባመረተው እየከበርን፣ በረሃ ላይ ፀሃይ እየበላው ባለው ወጣት ጥረት የሀይል ተጠቃሚ እየሆንን ቢያንስ ይህን እውነት ለመረዳት ለምን አልቻልንም?

መረዳቱ ቢያቅተን እናጥፋ፣ እንጥፋ፣ እምቢ እንበል የሚለውን የህሊና ሞራል ከየት አመጣን? በእርግጥ ይህ ሞራል የእኛ ነውን? አይመስልምና በጊዜ ከከፉው ህልምና ቅዠት እንመለስ። በዚህ የምንጀግን፣ ታሪክም የምንሰራ መስሎ ከታየን እውነትም ሞኞች ነን።

ጎበዝ ቀላል በሆነው ማጥፋት ጀግንነት የለም። ጀግና ከስራ የሚወለድ፣ ለህዝብ ጥቅም ዋጋ በመክፈል የሚያምን፣ በምክንያት የሚያስረዳ፣ በምክንያት የሚያሳምን፣ ከሞተም በምክንያት የሚሞት እንጂ እንደ ሞኙ ባለ ታሪክ «እምቢ» ብሎ ራሱ በሚያነደው ነበልባል የእሳት ራት የሚሆን አይደለም።

የኢትዮጵያ ህዝብ ደግሞ ይህን ሀቅ ጠንቅቆ ያውቀዋል፤ ያውቀናልም። ማን ምን እያደረገ እንደሆነ በብዕራችን ልክ ጭንቅላታችንን ከፍቶ ይመለከተናል። መሞት መኖራችንን ይነግረናል። «እነ ሞኞ» አሁን በሀገራችን እየታየ ያለው ልማት፣ ወደፊት ለእያንዳንዳችን መድረስ ያለበት እድገት፣ ከድህነት አምልጦ የመውጣት ሩጫ ያለ ህዝብ የመጣ ነው ብለን አምነን ይሆን? ህዝብ ሌት ተቀን የለፋበትን የድካም ውጤት አይጠብቀውም የሚል ግምገማስ ኖሮን ይሆን? እንዲያ ካሰብን እውነትም ሞተናል!